# ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
*2017/09*

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

---

**መጪውን ትውልድ መመገብ (Feed the Future Ethiopia) የእርሻ አገልግሎት ፕሮጀክት በባኮ ማዕከል ከፈተ**

**ባኮ፤ ኦሮሚያ፤ ኢትዮጵያ ግንቦት 4፤ 2009 -** አነስተኛ ማሣ ያላቸዉ አርሶ አደሮች ግብዓቶችን በቀላሉ እንዲያገኙ ለማስቻል በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ጥምረት የተቋቋመው የባኮ የእርሻ አገልግሎት ማዕከል ዛሬ  መጪውን ትውልድ መመገብ- ኢትዮጵያ (Feed the Future Ethiopia) የእርሻ አገልግሎት ፕሮጀክት ማዕከልን አስመረቀ፡፡ ማዕከሉ በፕሮጀክቱ ከሚከፈቱ ሌሎች 20 ተመሳሳይ ማዕከላት አንዱ ሲሆን በኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ፤ በፌደራልና በክልል የግብርናና የተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች ትብብር እንዲሁም በአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (ዩኤስኤአይዲ) የገንዘብና በካልቲቬቲንግ ኒው ፍሮንቲርስ ኢን አግሪካልቸር የቴክኒክ ድጋፍ ይተገበራል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት ተወካይ ስቴፈን ሞሪን የማዕከሉን ምርቃት አስመልክተው ባስተላለፉት መልዕክት እንዳሉት "ኢትዮጵያ ላቀደችው ሰፊ እና እጅግ የተለጠጠ የልማት አጀንዳ ተግባራዊነት፤ የግብርናው ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን ወሳኝ ድርሻ በውል መገንዘብ የሚጠይቅ ቢሆንም፤ ጥራት ያላቸውን የእርሻ ግብአቶች በተመጣጣኝ ዋጋ እና በትክክለኛው ጊዜ ማግኘት ትልቁ ችግር ነው፡፡"

የባኮ የእርሻ አገልግሎት ማዕከል ለባለ አነስተኛ ማሣ አርሶ አደሮች የግብርና ግብአቶችን ማድረስ አስቸጋሪ በሆነበት እና በኢትዮጵያ የበቆሎ መቀነት በሚባለው አካባቢ ይገኛል፡፡ አለሚቱ ሆርዶፋ በምትባል ሴት ሥራ ፈጣሪ ባለቤትነት የሚተዳደረው ማዕከሉ፤ አርሶ አደሮች ምርጥ ዘር፤ ኬሚካሎችን፤ የእርሻ መሣሪዎችን፤ የእንስሳት መድሃኒቶችን እና መሣሪያዎችን እንዲሁም የምክር አገልግሎት እና ስልጠናን የመሳሰሉ ጥራት ያላቸው የእርሻ ግብአቶችን በአንድ አከባቢ የሚያገኙበት ነው፡፡ እነኚህ አቅርቦቶች ባለ አነስተኛ ማሣ አርሶ አደሮች በዘላቂነት ምርታማነትንና የቤተሰብ ገቢን እንዲያሳድጉ ያግዛቸዋል፡፡ "የእኔ የእርሻ አገልግሎት ማዕከል ለአከባቢው ማኅበረሰብ ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ጠንካራ እምነት አለኝ፡፡ አርሶ አደሮች ጥራት ያላቸውን ሸቀጦች እና አገልግሎቶች በተመጣጣኝ ዋጋ እና በቅርበት እንዲያገኙ በማድረግ ችግራቸውን ይቀርፍላቸዋል" ስትል አልሚቱ ተናግራለች፡፡ "የእኔ የእርሻ አገልግሎት ማዕከል ከ10,000 ለሚበልጡ በባኮ እና አከባቢው ወረዳዎች የሚገኙ ባለአነስተኛ ማሣ አርሶ አደሮችን ሕይወት ይለውጣል" በማለት ጨምራ ገልጻለች፡፡

የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጄንሲ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሆኑት አቶ ካሊድ ቦምባ እንደገለጹት፤ "የባኮ እርሻ አገልግሎት ማዕከል መከፈት፤ የግሉን ዘርፍ የሚያሳትፍ አዲስ የአንድ መስኮት ግብአት ሥርጭትን ስኬታማነት ያበስራል፡፡" የአርሶ አደሮችን የግብአት እና አገልግሎት ጥያቄ ከማሟላት በዘለለ፤ የባኮን ማዕከል የመሳሰሉ የእርሻ አገልግሎት ማዕከላት፤ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እና አሰራሮችን ለማስፋፋት የሚያስችል መድረክ በመሆን ያገለግላሉ፡፡  መጪውን ትውልድ መመገብ- ኢትዮጵያ የእርሻ አገልግሎት ፕሮጀክት በኢትዮጵያ በግብርና ሥራ በሚታወቁ ክልሎች፤ በአማራ ስድስት፤ በኦሮሚያ አምስት፤ በደቡብ አራት እና በትግራይ ሦስት አካባቢዎች የእርሻ አገልግሎት ማዕከላትን በማቋቋም ላይ ይገኛል፡፡ እያንዳንዱ የእርሻ አገልግሎት ማዕከል የሚከፈተው በውድድር ሂደት አልፈው የተመረጡና እስከ 50,000 የአሜሪካን ዶላር የመነሻ ካፒታል የሚያሸንፉ ብቁ ሥራ ፈጣሪዎች ጋር በትብብር ይሆናል፡፡

በፕሮጀክቱ የመሳተፍ ዕድል የሚያገኙ ተወዳዳሪዎች፤ ፕሮጀክቱ በሚሰጣቸው ድጋፍ ታግዘው መሥፈርቱን የሚያሟላ ማዕከል ለማቋቋም ከሚያስፈልገው ካፒታል በትንሹ 50 በመቶውን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

መጪውን ትውልድ መመገብ (Feed the Future) ፤ 3.5 ቢሊዮን ዶላር የተመደበለት የዓለም አቀፍ የረሃብና የምግብ ዋስትና መርሐ-ግብር ሲሆን የአሜሪካ መንግሥት ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ መሠረት ለሆነው ግብርና የሚያደርገውን ድጋፍ ዘላቂነት እንዲኖረው በማድረግ ለሀገሪቱ ያለውን ትልቅ አጋርነት ያንጸባርቃል፡፡

###